በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የቅዱሳን አማላጅነት - መግቢያ


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## የካቲት ፳፬ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

# አማላጅነት

*በዚህ ርዕስ የሚከተሉትን እንመለከታለን።*

1. የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂነትና የቅዱሳን አማላጅነት ልዩነት
2. የቅዱሳን አማላጅነት ማለት ስለእኛ ይጸልዩ ዘንድ መጠየቅ መሆኑን
3. ሰዎች የቅዱሳንን አማላጅነት እንዲጠቀሙ እግዚአብሔር መጠየቁን
4. መላዕክትና ቅዱሳን በምድር ስላለንበት ሁኔታ ያውቃሉ?
5. የቅዱሳን ታላቅነት፣ ዕውቀትና አገልግሎታቸው
6. ስለ ቅዱሳን ታላቅነት የሚያስረዱ ሌሎች ምሳሌዎች
7. በሥጋ ያረፉ ቅዱሳን አሁንም በሕይወት ያሉ ስለመሆናቸው
8. የመላዕክት አማላጅነት ምሳሌዎች
9. ቅዱሳን በጌታችን ዘንድ ያላቸው ክብር
10. የቅዱሳንን አማላጅነት የመጠየቅ መንፈሳዊነት
11. አማላጅነት ያለ እውነታ ስለ መሆኑ
12. ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

# የአማላጅነት ትምህርት መግቢያ

## ***የትምህርቱ ዓላማ***

- የቅዱሳንን አማላጅነት አስፈላጊነት መረዳት ነው፡፡

## ***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ***

-"… እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡" ***ያዕ 5፡16፡፡***

## ***የሚነበቡ መጻሕፍት***

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ታሪክ - ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ፣ ትምህርተ መለኮት - አሥራት ገ/ማርያም፣…

***መግቢያ***

-ወላጆቻችንን ቅርብ የሆኑ ወዳጆቻችንን፣ እህት/ወንድማችንን ለእኛ ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ቢጠይቁልን ስህተት ነው?

- ጌታችን በሥጋ ወራት ስለ ኃጢአታችን ሥርየት ዕዳችንን በመክፈል፣ ስለኛ ደሙን በማፍሰስ፡ በመሞት የዕዳ ደብዳቤያችንን በመደምሰስ ራሱ ታርቆን ከባሕርይ አባቱና ከባሕርይ ሕይወቱ አስታርቆናል፡፡

- "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ፡፡" ***ኢሳ 53፡6***፣ "በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት…" ***ኤፌ 1፡7***፣ "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን…" ***ራዕ. 1፡5***፣ "ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፡፡" ***ቆላ 1፡22***፣ "እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፡፡" ***ዕብ 5፡7፡፡***

# የቅዱሳን አማላጅነት - ስለኛ መጸለይ ነው!

1. ከጌታችን (እግዚአብሔር) ወልድ ማስታረቅ የተለየ ነው፡፡

2. "… እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡" *ያዕ 5፡16፡፡*

3. ቅዱሳንም ሰዎች ይጸልዩላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ "በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን *ስለ እኛ ጸልዩ፡፡*" *2ኛ ተሰ 3፡1፡፡*

4. "ጸልዩልን…" *ዕብ 13፡18፡፡*

5. "በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፡፡" *ኤፌ 6፡18-19፡፡*

6. ታዲያ እንደኛ ባለ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያሉትን ጸልዩልን ብለን የምንጠይቅ ከሆነ የዚህን ዓለም ውጊያና ፈተና በድል ተወጥተው የፈጸሙትንና በገነት የሚገኙትን ቅዱሳን ጸልዩልን ብለን መጠየቅ የለብንም???

   - "እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፥ ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፡፡" *ዕብ 11፡33*

   - "እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡፡" *ራዕይ 3፡21*

   - "በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር የሚመስለውን አየሁ፥ በአውሬውና በምስሉም በስሙም ቍጥር ላይ ድል ነሥተው የነበሩት የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባሕር ላይ ሲቆሙ አየሁ፡፡" *ራዕ 15፡2፡፡*

# እግዚአብሔር የቅዱሳንን አማላጅነት እንድንጠቀም ጠይቆናል !

1. ***አብርሃምና ንጉሥ አቤሜሌክ፡ -*** “አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ።” ***ዘፍጥ 20፡7።***

2. ***ኢዮብና ሦስቱ ጓደኞቹ፡-*** “እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቍጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል። አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፥ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፥ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና።” ***ኢዮ 42፡7-8።***

3. ***በሁለቱም ክስተቶች እግዚአብሔር ራሱ የበደሉትን ሰዎች በቀጥታ ተናግሯቸዋል፡ -*** የኃጢአታቸውንም ሥርየት በቀጥታ አልሰጣቸውም። የኃጢአታቸውን ሥርየት እንዲያገኙ ቅዱሳኑ ይጸልዩላቸው ዘንድ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠላቸው፣ ቅዱሳኑም በሰው ሁሉ ፊት በሁለቱም በደለኞች ፊታቸው ክብር እንዲደገኙ አድርጓል።

4. ***አብርሃምና ስለ ሰዶም ያቀረበው ምልጃ፡ -***

   - “እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?” ***ዘፍጥ 18፡17።***

   - “አብርሃምም ቀረበ አለም። በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን? አምሳ ጻድቃን በከተማይቱ ውስጥ ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን? ከተማይቱንስ በእርስዋ ስለሚገኙ አምሳ ጻድቃን አትምርምን? ይህ ከአንተ ይራቅ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ትገድል ዘንድ፥ ጻድቁም እንደ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ። የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን? እግዚአብሔርም፦ በሰዶም በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለ እነርሱ እምራለሁ አለ። አብርሃምም መለሰ አለም። እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆ አንድ ጊዜ ጀመርሁ ከአምሳው ጻድቃን አምስት ቢጐድሉ ከተማይቱን ሁሉ በአምስቱ ምክንያት ታጠፋለህን? ከዚያ አርባ አምስት ባገኝ አላጠፋትም አለ። ደግሞም ተናገረው፥ እንዲህም አለ፦ ምናልባት ከዚያ አርባ ቢገኙሳ? እርሱም፦ ለአርባው ስል አላደርገውም አለ። እርሱም፦ ጌታዬ አይቆጣ እኔም እናገራለሁ ምናልባት ከዚያ ሠላሳ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም ከዚያ ሰላሳ ባገኝ አላጠፋም አለ። ደግሞም፦ እነሆ፥ ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ አንድ ጊዜ ጀመርሁ ምናልባት ከዚያ ሀያ ቢገኙሳ? አለ። እርሱም፦ ከዚያ ሀያ ቢገኙ ስለ ሀያው አላደርገውም አለ። እርሱም፦ እኔ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ብናገር ጌታዬ አይቆጣ ምናልባት ከዚያ አሥር ቢገኙሳ? አለ። እርሱም፦ ስለ አሥሩ አላጠፋትም አለ።” ***ዘፍጥ 18፡23-32።***

# እግዚአብሔር የቅዱሳንን አማላጅነት እንድንጠቀም ጠይቆናል !

## *5. ሙሴ ስለ እስራኤል ሕዝቦች ያደረገው ምልጃ፡ -*

- ሕዝቡ የወርቁን ጥጃ አምልከዋልና እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያጠፋ ፈለገ፡፡

- ሊያደርገው የፈቀደውንም ቀጥታ አልፈጸመውም ለወዳጁ ለነቢዩ ሙሴ አማከረው፣ ስለ ሕዝቡም ያማልድ ዘንድ ዕድል ሰጠው፣ ሙሴም በዕድሉ ተጠቅሞ አማለዳቸው እግዚአብሔርም ተቀበለው፡፡

- *"እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ከግብፅ ምድር ያወጣኸው ሕዝብህ ኃጢአት ሠርተዋልና ሂድ፥ ውረድ፡፡ ካዘዝኋቸው መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል ለራሳቸው አደረጉ፥ ሰገዱለትም፥ ሠዉለትም፡፡ እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አሉ ሲል ተናገረው፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት፥ እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፡፡ አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ አለው፡፡ ሙሴም በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ጸለየ፥ አለም፡፡ አቤቱ፥ ቍጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ? ግብፃውያንስ፡፡ በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለ ምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ፥ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ፡፡ ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፥ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ፥ ለዘላለምም ይወርሱአታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ፡፡ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ፡፡"* ***ዘፍጥ 32፡7-14፡፡***

# በሥጋ ያረፉ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዘንድ የበለጠ ክብር አላቸው!

1. ***ንጉሥ ሰሎሞን በበደለ ጊዜ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለመክፈል ፈለገና እንዲህ አለው፡ -***
“እግዚአብሔርም ሰሎሞንን አለው። ይህን ሠርተሃልና፥ ያዘዝሁህንም ቃል ኪዳኔንና ሥርዓቴን አልጠበቅህምና መንግሥትህን ከአንተ ቀዳድጄ ለባሪያህ እሰጠዋለሁ። ነገር ግን ከልጅህ እጅ እቀድደዋለሁ እንጂ ስለ አባትህ ስለ ዳዊት ይህን በዘመንህ አላደርግም። ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ለልጅህ አንድ ነገድ እሰጣለሁ እንጂ መንግሥቱን ሁሉ አልቀድድም።” *ቀዳ ነገ 11፡11-13፡፡፡፡*

2. ***እግዚአብሔር ኢዮርብዓምን ባነጋገረውም ጊዜ ይህንኑ ቃል ደግሞታል፡-*** “ኢዮርብዓምንም አለው። አሥር ቍራጭ ውሰድ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ ከሰሎሞን እጅ መንግሥቱን እቀድዳለሁ፥ አሥሩንም ነገዶች እሰጥሃለሁ። ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊት ከእስራኤልም ነገድ ስለ መረጥኋት ከተማ ስለ ኢየሩሳሌም ግን አንድ ነገድ ይቀርለታል። ጥለውኛልና፥ ለሲዶናውያንም አምላክ ለአስታሮት፥ ለሞዓብም አምላክ ለካሞሽ፥ ለአሞንም ልጆች አምላክ ለሚልኮም ሰግደዋልና፥ አባቱም ዳዊት እንዳደረገ በፊቴ ቅን ነገር ያደርጉ ዘንድ፥ ሥርዓቴንና ፍርዴንም ይጠብቁ ዘንድ በመንገዴ አልሄዱምና። መንግሥቱንም ሁሉ ከእጁ አልወስድም ትእዛዜንና ሥርዓቴን ስለ ጠበቀው ስለ መረጥሁት ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊት ግን በዕድሜው ሁሉ አለቃ አደርገዋለሁ።” *ቀዳ ነገ 11፡31-34፡፡*

***ስለዚህ ሰዎች ከዚህም ዓለምም ይሁን ከወዲያኛው ዓለም የሚጸልዩት ጸሎት***

1. በሰው ልጆች መካከል ያለን ጽኑ ፍቅር ይገልጣል፡፡ *ዕብ 11፡1-40፡፡*
2. በሥጋ የተለዩት በሕይወት ይኖራሉ፣ ጸሎታቸውም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለ ብለን የማመናችን ማረጋገጫ ነው፡፡ “በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል።” *ሮሜ 2፡7*
3. እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ከፍ ፈፈለ ክብር የሰጣቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ “ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ።” *ቀዳ ጴጥ 4፡14*፣ “እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።” *ካል ቆሮ 3፡18፡፡*

# <u>የቅዱሳን አማላጅነት!</u>

1. ***<u>መላዕክትና በሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን እኛ በምድር ያለንበትን ሁኔታ ያውቃሉ?</u>***

- በሰማይ ያለው ዕውቀት በምድር ካለው ይበልጣል፡፡ "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን *<u>በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን</u>*፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ *<u>በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ</u>*፡፡" *<u>ቆዳ ቆሮ 13፡12፡፡</u>*

- የመላዕክት ዕውቀታቸውን አስመልክቶ "እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ *<u>በሰማይ ደስታ ይሆናል</u>*፡፡" *<u>ሉቃ 15፡7፡፡</u>*

- መላዕክት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ጸሎታችንን የሚያሳርጉልን ናቸውና የምንጸልየውን ጸሎት ያውቃሉ፡፡ "ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡" *<u>ራዕ 8፡3-4፡፡</u>*

2. ***<u>በሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን እኛ በምድር ያለንበትን ሁኔታ ያውቃሉ?</u>***

*<u>የአብርሃም፣ የባለጠጋው ነዌና የድሃው አልአዛር ታሪክ፡-</u>*

- አባታችን አብርሃም ባለጠጋውን "ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ፡፡" አለው፡፡ *<u>ሉቃ 16፡25-31፡፡</u>*
- አባታችን አብርሃም አልአዛር በምድር ሳለ ክፉን እንደተቀበለ እንዴት አወቀ?
- አባታችን አብርሃም ባለጠጋው ነዌ በምድር ሳለ መልካም እንደተቀበለ እንዴት አወቀ?
- አብርሃም ከሙሴና ከነቢያቱ ብዙ መቶ ዓመታት አስቀድሞ ያረፈ ሆኖ የባለጠጋው ቤተ ሰዎች ሙሴና ነቢያት እንዳሉአቸው እንዴት አወቀ? ይህን ሁሉ አብርሃም እንዴት አወቀ?
- ጌታችን "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው፡፡" ያለለት አብርሃም … በዕረፍት ሥፍራ ሆኖ የሚደረገውን አያውቅም? አወቀ እንጂ…

# <u>የቅዱሳን አማላጅነት!</u>

***<u>አስደናቂው የነቢዩ የኤልያስ ታሪክ፡-</u>***

- በካልዕ ዜና መዋዕል እንደተጻፈው ኢዮራም በይሁዳ ሲነግስ ወንድሞቹንና የእስራኤልን መሳፍንት በሰይፍ ገደለ፣ በአክዓብም የክፋት መንገድ ሄደ፣ በእግዚአብሔር ላይ አመጸ፣ በይሁዳ ተራሮች ላይ መስገጃዎችን ሠራ፥ በኢየሩሳሌምም የተቀመጡትን እንዲያመነዝሩ አደረጋቸው፥ ይሁዳንም አሳተው። ***<u>ካል ዜና 21፡1-11።</u>***

- በመቀጠልም ከብዙ ዘመናት በፊት ወደ እግዚአብሔር ከተወሰደው ከኤልያስ የተላከለትን ደብዳቤ ተቀበለ። ከነቢዩ ከኤልያስ ተልኮለት የተቀበለውም ጽሕፈት እንዲህ የሚል ነበር፡- "የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በአባትህ በኢዮሣፍጥ መንገድ በይሁዳም ንጉሥ በአሳ መንገድ አልሄድህምና፥ በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ግን ሄደሃልና፥ የአክዓብም ቤት እንዳደረገ ይሁዳንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን እንዲያመነዝሩ አድርገሃልና፥ ከአንተም የሚሻሉትን የአባትህን ቤት ወንድሞችህን ገድለሃልና። እነሆ፥ እግዚአብሔር ሕዝብህንና ልጆችህን ሚስቶችህንም ያለህንም ሁሉ በታላቅ መቅሠፍት ይቀሥፋል።" ***<u>ካል ዜና 21፡12-14።</u>***

- ይህ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ኤልያስስ ከምድር ከነሠረገላው ከተወሰደ በኋላ የሚደረገውን ነገር እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

***<u>ማጠቃለያ</u>***

- አማላጅነታቸውን ለመጠየቅ ወደ ቅዱሳን እንጸልያለን።
- በጸሎታችንም ይጸልዩልንና ይረዱን ዘንድ እንጠይቃለን።
- ወደ እመቤታችን የምናቀርበው ከልጆች ወደ እናት የሚቀብ ጥያቄ ነው - ይኸውም የልባችን ምስጢር ነው።
- ራሱ እግዚአብሔር የፈቀደውና እናደርገውም ዘንድ ያመለከተን ነው።
- አቤሜሌክ በሕይወት ይኖር ዘንድ አብርሃም እንዲጸልይለት አመልክቶታል። ዘፍጥ 20፡7።
- የኢዮብንም ጓደኞች "ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፥ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና።" ብሎ አዝዞአቸዋል። ***<u>ኢዮብ 42፡8።</u>***
- አብርሃም ስለ ሰዶም፣ ሙሴ ስለ እስራኤል፣ ይጸልዩ ዘንድ ፈቅዶላቸዋል። ልመናቸውንም ሰምቶ ተቀብሎአቸዋል። ***<u>ዘፍጥ 18፣ ዘጸ 43።</u>***

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።